# የገቢ ግብር ነፃ መብቶች

# አፈጻጸም መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈጻጸም መመሪያ ቁ 21/2001

መንግሥት ከገቢ ግብር ነፃ የሚሰጠውን መብት በአዋጁ መሠረት አግባብ ባለው ሁኔታ ማስፈፀም በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 27 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 21/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የመዘዋወሪያ አበል" ማለት አሰሪው ወይም ቀጣሪው ከሠራተኛው ወይም ከተቀጣሪው ጋር ባለው የስራ ውል መሠረት ለሠራተኛው የሚከፈለው አበል ነው፡፡
2. "ከግብር ነፃ የመዘዋወሪያ አበል" ማለት በአዋጁ ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት ከሚጣለው ግብር ነፃ የተደረገ አበል ነው፡፡
3. "የታክስ ማዕከል" ማለት የባለሥልጣኑ ገቢ ሰብሳቢ አካል ነው፡፡
4. "ኩባንያ" ማለት የአክሲዮን ማኀበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር ነው፡፡
5. "የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ" ማለት የአክሲዮን ባለቤት የሆኑ ሰዎች ኩባንያው ከሚያገኘው ትርፍ በአክሲዮናቸው መጠን የሚያገኙት ገቢ ነው፡፡
6. "የተለየ ተግባር" ማለት ለአንድ ሰው፣ ለህዝብ ወይም ለተቋም የሚፈፀም የተለየ ውጤት የሚያስገኝና በተቋሙ ሙሉ እውቅና የተሰጠው ድርጊት ነው፡፡
7. "አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ነው፡፡
8. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
9. "ሚኒስትር" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ መሠረት ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ከግብር ነፃ ስለሆነ የመዘዋወሪያ ወይም የአየር ፀባይ አበል

1. የመዘዋወሪያ አበል ከግብር ነፃ እንዲሆን የሚፈቀደው በአሠሪው /ቀጣሪው/ እና ተቀጣሪው ወይም ሠራተኛው መካከል በተደረገው የስራ ውል ውስጥ በግልጽ በተመለከተ እና በስራ ፀባይ ምክንያት በመዘዋወር ለሚከናወን ተግባር ሲውል ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የመዘዋወሪያ አበል ቀጣሪው በሚመድበው ተሽከርካሪ ለሚጠቀሙና ከመኖሪያ ወደ ስራ ቦታ እንዲሁም ከሥራ ቦታ ወደ መኖሪያ ቤት ለመሄድ የሚደረገውን የትራንስፖርት ወጪ አያካትትም፡፡
3. በወር ውስጥ ከግብር ነፃ የሚደረገው የመዘዋወሪያ አበል መጠን ከሠራተኛው ጠቅላላ ደመወዝ እስከ አንድ አራተኛ ($\frac{1}{4}$) ድረስ ብቻ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ከብር 1000.00 /አንድ ሺህ/ አይበልጥም፡፡
4. አንድ ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ከ25 ኪ.ሜ ርቀት በላይ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚከፈለው የአንድ ቀን ውሎ አበል እስከ ብር 150 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ የሚደርስ ሆኖ ወይንም በማንኛውም ሁኔታ የደመወዙን 4% አይበልጥም፡፡
5. አንድ ሠራተኛ ከተቀጠረበት ወይም ከነበረበት ቦታ ወደተመደበበት የሥራ ቦታ ሲሄድ ወይንም ሥራውን አጠናቆ ወደ ምድብ ቦታው ሲመለስ በሥራ ውሉ መሠረት የሚታሰብለት የትራንስፖርትና መጓጓዣ ወጪ በሚያቀርበው የወጪ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ወጪው በሥራ ላይ ካለው የአየርና የየብስ ትራንስፖርት ታሪፍ ሊበልጥ አይችልም፡፡
6. አንድ የውጭ አገር ዜጋ አገር ውስጥ ገብቶ በመሥራት የኮንትራት ዘመኑን ጨርሶ ወደ አገሩ ሲመለስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ በተፈፀመው የቅጥር ውል መሠረት እና የአየርና የየብስ ትራንስፖርት ታሪፍ ግምት ሆኖ የጓዙ ክብደት ከ300 ኪ.ግ. አይበልጥም፡፡
7. በረሃማነታቸው በሕግ በግልጽ ለተቀመጡ አካባቢዎች የሚከፈል የአየር ፀባይ አበል፡፡

## 5. የአሠሪው ወይም የቀጣሪው ግዴታ

በዚህ መመሪያ መሠረት ከግብር ነፃ ከተደረገው መጠን በላይ የሚከፍል አሠሪ ወይንም ቀጣሪ ክፍያውን በተቀጣሪው ደመወዝ ላይ በመደመር በአዋጁ መሠረት ግብሩን ቀንሶ ለታክስ ባለሥልጣኑ በየወሩ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. ከግብር ነፃ ስለተደረገ የመኖሪያ ቤት መተላለፍ

የመኖሪያ ቤት ወደ ሌላ ወገን በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ ሲተላለፍ ከግብር ነፃ የሚሆነው ቤቱ የሚገኝበት ቀበሌ አስተዳደር ቀደም ሲል ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ማገልገሉን በማስረጃ ሲያረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## 7. አዲስ የፈጠራ ሀሳብ በማቅረብ በሽልማት የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ስለሚሆንበት ሁኔታ

1) አንድን ቴክኖሎጂ በማሻሻል ወይም አዲስ ግኝት በመፍጠር ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል አሠራር ሥራ ላይ በማዋል ምክንያት፣ እንዲሁም የተለየ ተግባር ላከናወነ ሰው የሚሰጥ ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆነው ሽላሚው ድርጅት ለዚህ ውሳኔ የደረሰበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ ሲሰጥና የማስረጃው ትክክለኛነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተመለከተው መሠረት የሚቀርብ ማስረጃ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ከገቢ ግብር ክፍያ ነፃ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 8. ካፒታልን ለማሳደግ የዋለ የአክሲዮን የትርፍ ድርሻን ከገቢ ግብር ነፃ ስለማድረግ

1. *መሠረቱ*

   የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚያዝያ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. በቁጥር አመ3/16/28/100 በፃፈው ደብዳቤ ባለሥልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር የሚመለከቱ የኢንቨስትመንት መስኮች፣ ባለሀብቶች ያገኙትን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ካዋሉ ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆኑ ወስኗል፡፡

2. **ከትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር ነፃ የሆኑ የሥራ ወይም የኢንቨስትመንት መስኮች፡-**

ከዚህ በታች በተመለከቱ የሥራ መስኮች ከተሰማሩ ኩባንያዎች በስተቀር በሌሎች የሥራ መስኮች የተሰማሩ ኩባንያዎች የአክሲዮን ባለሀብቶች ያገኙት የትርፍ ድርሻ የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት ሊከፈል ከሚገባው ግብር ነፃ ይሆናሉ፡፡

ሀ/ ባለኮከብ ደረጃዎችን የማይጨምሩ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ፔንሲዮኖች፣ ሻይ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የምሽት ክበቦች፣ ዓለም አቀፍ ደረጃ የሌላቸው ሬስቶራንቶችና ምግብ ቤቶች፣

ለ/ የንግድ ሥራዎች ማለትም የጅምላ፣ የችርቻሮ እና አስመጪነት ሥራ፣

ሐ/ የጥገና አገልግሎት ሥራ፣

መ/ የንግድ መንገድ ትራንስፖርትና የመኪና ማከራየት አገልግሎት ሥራ፣

ሠ/ የፖስታና ኩሪየር አገልግሎት ሥራ፣

ረ/ ለንግድና ለመኖሪያ የሚሆኑ ቤቶችና ሕንፃዎችን ሠርቶ ማከራየትና መሸጥ፣

ሰ/ የአማካሪነት ሥራ፣

ሸ/ የማስታወቂያ ሥራ፣

ቀ/ የፊልምና መሰል ሥራዎች፣

በ/ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ሥራ፣

ተ/ የሲኒማና ቲያትር ቤቶች አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ቸ/ የጉምሩክ አስተላላፊነት ንግድ ሥራ፣

ኀ/ የላውንደሪ አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ነ/ የጉዞ ወኪልነት፣ የንግድ ረዳትና የትኬት መሸጫ አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ኘ/ የሎተሪና የመሳሰሉ ሥራዎች፣

3. **የኩባንያው ኃላፊነት**

በአዋጁ አንቀጽ 34 በተደነገገው መሠረት ኩባንያው ለባለአክሲዮኖች የሚያከፋፍለውን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ በአዋጁ አንቀጽ 54(3) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ፡-

ሀ/ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚደርሰውን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ መጠን፣

ለ/ ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ትርፍ ድርሻቸውን የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ እንዲውል የወሰኑ መሆናቸውን የሚገልጽ የፀደቀ ሰነድ፣

ሐ/ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻው የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ በመዋሉ ምክንያት የኩባንያው ካፒታል በምን ያህል መጠን እንዳደገ የሚያብራራ መግለጫ፣

ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 9. ሌሎች ከግብር ነፃ ስለሚደረጉ ገቢዎች ወይም ሰዎች

1. በአዋጁ ነፃ የተደረጉ ገቢዎችና በዓለም አቀፍ ስምምነትና እንዲሁም ሚኒስትሩ ከገቢ ግብር ነፃ ያደረጋቸውና የሚያደርጋቸው ገቢዎች ወይንም ድርጅቶችና ግለሰቦች ከግብር ነፃ ይስተናገዳሉ፡፡

2. በዕድል ሙከራ እስከ ብር 100 የሚገኙ ገቢዎች ከግብር ነፃ ይስተናገዳሉ፡፡

## 10. ስለ ግብር ነፃ ገቢዎች መረጃ

በሕግ ወይም በሚኒስትሩ ነፃ የተደረጉትን ገቢዎች ወይም ድርጅቶች፣ ግለሰቦች እንዲሁም ሊከፈል የነበረውን ግብር መጠን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ዝርዝር መረጃ ይይዛል፣

## 11.የተሻሩ መመሪያዎች

ቀደም ሲል ከግብር ነፃ መብቶችን አፈፃፀም በተመለከተ በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎች በዚህ ተተክተዋል፡፡

## 12.የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ------------ /2001 ዓ.ም

መለኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር